ያ ትውልድ

የ«ያ ትውልድ ተቋም» ልሳን

ያ ትውልድ ቅጽ 7 ቁጥር 3 የካቲት ፳፱ ቀን ፪ ሺህ ፲፪ ዓ.ም.


# የያ ትውልድ ሴቶች ትውስታና የእናቶች ሰቆቃ

*(ማርች 8 ዓለም አቀፍ የሴቶች ቀን 109ኛ ዓመት ምክንያት በማድረግ)*

እንኳን ለዓለም አቀፍ የሴቶች ቀን ማርች 8 109ኛ ዓመት አደረሳችሁ፣ አደረሰን መልዕክታችን ከ«ያ ትውልድ ተቋም» ይድረሳችሁ። ማርች 8 ስናስታውስ በሴቶች ላይ የደረሰውን ስቃይ፣ ግፍ፣ ሰቆቃ፣ ጭቆና፣ እንግልት፣ ስደት በዓይነ ኅሊናችን እንስላለን። ማርች 8 ስናስታውስ የሴቶችን ጥንካሬ፣ ተጋድሎ፣ ጥበብ፣ አመራር እናስባለን። ማርች 8 ስናስታውስ በሀገራችን ኢትዮጵያ መከበር ከጀመረበት 1968 ዓ.ም. ወቅት ሴቶች ለመብታቸው ካደረጉት ተጋድሎ አድማሱን አስፍቶ ለሀገራቸውና ለሕዝባቸው ዴሞክራሲያዊ መብት እውን መሆን የከፈሉትን አኩሪ ትግልና መስዋዕትነት አንዘነጋውም። ማርች 8 ስናስታውስ በአረመኔው የደርግ ቀይ ሽብር ሰለባ የሆኑትን ብርቅዬ ወጣት ሴቶችን ከፍ እናደርጋቸዋለን። ማርች 8 ስናስታውስ  በአረመኔው የደርግ አገዛዝ ልጆቻቸውን በቀይ ሽብር ተነጥቀው የተንገላቱ፣ የተሰቃዩ፣ እየዬ ብለው ያልወጣላቸውን ዕድሜአቸውን በሰቀቀን፣ በቁጭትና በፀፀት የገፉትን የኢትዮጵያን እናቶች አልዘነጋናችሁም እንላቸዋለን። ማርች 8 ስናስታውስ ለሀገራችን ሉዓላዊነት በዱር በገደሉ የተንከራተታችሁና ኢትዮጵያችንን ከወራሪና ከጠላት ለመከላከል ትልቁን ድርሻ የተወጣችሁ እናትና ወጣት አርበኞች ክብር ለናንተ እንላለን። ማርች 8 ስናስታውስ በኢሕአዴግ/ወያኔ አገዛዝ በግፍ ለተሰቃያችሁ፣ በእሥር ለማቀቃችሁ፣ በስደት ለተንገላታችሁ፣ ለተገደላችሁ እናቶችና እህቶች አሁንም ልጆቻችሁን አጥታችሁ፣ ታፍነውባችሁ እየዬያችሁ ያላባራ እናቶች፣ ከቀዬሃችሁ በመፈናቀል እስካሁን ለአስከፊ እንግልት ለተዳረጋችሁ እናቶችና፣ እህቶች ብሶታችሁ ብሶታችን፣ ሀዘናችሁ ሀዘናችን መሆኑን እንገልጽላችኋለን።

ከተመሰረተ ስምንተኛ ዓመቱን በመጪው ሰኔ 2012 ዓ.ም. የሚያከብረው “ያ ትውልድ ተቋም” የዘንድሮውን ማርች 8 ክብረ በዓል ምክንያት በማድረግ  በየዓመቱ ካስነበብናቸው አጠናክረን የሴቶች እናቶችንና ወጣቶችን አኩሪ ተጋድሎ፣ አሳዛኝ ፍጅትና መሪር ሀዘን ዳግም ልናስነብብ ወደድን። የቀይ ሽብር ፖሊሲ አውጪዎችና ገዳዮች ዛሬም ፀፀት ያላገኛቸው የታሪክ በራዥነታቸው ተከላካይ ያስፈልገዋልና ተጽፎ ከማያልቀው የግፍ ማህደራቸው ማርች 8 አስመልክቶ ትውልድ ያውቀው ዘንድ፣ በመረጃነት ያገለግል ዘንድ፣ ሌሎችም የሚያውቁትን ይጽፉ ዘንድ ያልተነገረላቸውን ሴቶች፣ ድምጽ አልባ ሆነው የተደፉትን የያ ትውልድ እንስቶች እናስታውስ ዘንድ ያቅማችንን ታሪካቸውን፣ ገድላቸውን እንደግምላቸዋለን።

ታሪክ ነውና በኢትዮጵያ የትግል ታሪክ በቅድመ የካቲት 1966 ዓ.ም. አብዮት ተደራጅቶ በየካቲት አብዮት ማግስት ለሕዝብ ብቅ ያለው የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ (ኢሕአፓ) ሴቶች

እህቶቻችንን በትግሉ በማሳተፍ የኢትዮጵያ ልጆች ያላቸውን የሀገርና ሕዝብ ፍቅር በእህቶቻችንና በእናቶቻችን ዘንድ ምን ያህል እንደተተገበረ ያሳየ የቀዳማይ እመቤቶች ፓርቲ ነበር ቢባል ይገባዋል። ኢሕአፓ ሴቶችን ለመብታቸው ብቻ ሳይሆን ለሀገርና ለሕዝብ መብት ይሚገቱ ዘንድ "እነሆ ተከተሉኝ!" ሲል መቀነታቸውን አጥብቀው የጎረፉለት እናቶቻችን፣ እህቶቻችን ትብብርና ድጋፍ ሊታመን ከሚገባው በላይ ውብ ነበር። በድል አድራጊነት የሴቶች እኩልነትን ለማሳየት ኢሕአፓ ዕጣው ባይገጥመውም በትግሉ የሴቶችን ማንነትና ጀግንነት ያሳየና ከወንድ እኩል አይደለም በላይ አመራራቸውና ጀግንነታቸው የተመሰከረላቸው በርካታ የትግል እመቤቶች በታሪክ መዝገቡ አስፍሯል። ወጣት ሴቶች በመሪ አታጋይ ፓርቲያቸው ኢሕአፓ ጥላ ሥርና በኢትዮጵያ ሴቶች ትግላዊ ድርጅት (ኢሴትድ) አማካይነት ከወንዶች እኩል ታግለዋል፣ አታግለዋል የፋሽስት ደርግን አሰቃቂ ስቃይና፣ መከራ ተቀብለዋል።

እናቶች ለኢሕአፓ ልጆች የምስጢር ጓዳ በመሆን በርካታ ተግባራት አከናውነዋል። የጠላትን መውጫ መግቢያ በመጠባበቅ ዘብ ቆመዋል። የገበያ ዘምቢላቸውን ለኢሕአፓ ሠነዶች አውለዋል። መክተፊያቸውን ለ"አደፍርስ" ማባዣ ጠለላ ሰጥተዋል። የቤት አጥሮቻቸው ወቅታዊ መፈክሮችን አስተናግደዋል። ቤታቸውን ለኢሕአፓ ተግባራዊ ሥራ ሰጥተዋል። በፋሽስቱ ደርግ ቀይ ሽብር ዘመንም በእናትነታቸው ሳይከበሩ ታስረዋል፣ ተገርፈዋል፣ ተገድለዋል። ለልጆቻቸው ስቃይና ሞት አልቅሰው አልወጣላቸውም፣ የቁም መከራን እስከ ዕድሜያቸው ፍጻሜ ያስተናገዱ በርካቶች ናቸው። በከተሞች በየቀበሌውና ከፍተኞች፣ በየክፍላተ ሀገሩ በወረዳና አውራጃ ጭምር ብዕር ያላገኘው፣ ያልተዘገበው አስደናቂና በስተመጨረሻም መሪር ታሪካቸው ቀላል አይደለም።

ማርች 8 በኢትዮጵያ ይከበር ዘንድ የሴቶች ትግል ውጤት ነው። ዕለቱ ሴቶች ከመብታቸው በላቀ መልኩ ለሀገራቸውና ሕዝባቸው አንድነትና እኩልነት ያደረጉትንና የሚያደርጉትን ተጋድሎ የሚያስቡበትና የሚያጠናክሩበት ነው።

በየካቲት 1966 አብዮት ወቅትና ከዚያም በኋላ ሴቶች ግንባር ቀደም ሆነው አረመኔውን የደርግ አገዛዝ ታግለዋል። የትግል ጓዳ እናቶች የከተማው ትግል አስተዋጽዖ አስደናቂ ነበር። ሴቶች በትግሉ አስከፊውን የፋሽስቶች ዱላና መከራ አስተናግደዋል። ኢሰብአዊ በሆነ መንገድ የደርግ ገራፊዎችና ገዳዮች ስሜት ማርኪያ በመሆን የስነልቦናዊና የአካል ጥቃት ሰለባ ሆነዋል። እስከወዲያኛው በፋሽስት አውሬዎች ተበልተዋል። "ትግል ሕይወቴ" ብላችሁ ለሀገርና ለህዝብ ላይ ታች እንዳላችሁ በግፈኞች እጅ ወድቃችሁ፤ አካላችሁ ተተልትሎ በስቃይ ያንቀላፋችሁ የያ ትውልድ እንስት አባላት ታሪክ ሰርተው ካንቀላፉ እህቶቻችን ማዕከል ናችሁና በማርች 8 ክብር ለእናንተ እንላለን።

***<u>ከበርካታ የግፍ ሰለባ ሴቶች ጥቂቶቹ፦</u>***

***<u>ዳሮ ነጋሽ፦ ዐመጽ ያጋተው ጡትሽ አልነጠፈም !</u>***



ዳሮ ነጋሽ
Daro Negash

በጨካኝ ፋሺስቶች በትር የተዘረረችው የዘጠኝ ወር ነፍሰ ጡሯ ዳሮ ነጋሽ ልጆችሽ አለን፤ ዐመጽ ያጋተው ጡትሽ አልነጠፈም ! እንላታለን።

"መጋቢት 14 ቀን 1969 ዓ.ም. ከጠዋቱ አራት ሰዓት አካባቢ አረመኔው ግርማ ከበደ ከአጃቢዎቹ ጋር ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት ሰተት ብሎ ገብቶ ሠራተኞቹን ለስብሰባ እንደሚፈልግ ተናገረ። …ከተሰበሰበው ሰራተኛ መሀል የስም ዝርዝሩን እያነበበ አስወጣ። ዘጠኝ ብቻ ተገኙ።

*ዳሮ ነጋሽ ከዘጠኙ መሀል አንዷ ብትሆንም ስብሰባው ላይ አልነበረችም። እስር ቤት ለሚገኘው ባሏ ስንቅ አቀብላ አርፍዳ ስትመጣ የውጭ በር ላይ ጠብቀው ነው የያዟት።…*


*መጋቢት* 15 *ቀን* 1969*ም ዓ.ም. አዲስ ዘመን ጋዜጣ "…በማተሚያ ቤቱ ሐቀኛ ተራማጆችና በቀበሌ* 07 *ታጋይ ጓዶች የተጋለጡት ቀንደኛ ፀረ አብዮተኞች በቁጥጥር ሥር ውለዋል።" የሚለውን ዜና ይዞ ወጣ።*

*ጋዜጣው ይህንን ዜና ይዞ በወጣበት ዕለት ዘጠኙ ሠራተኞች ቀድመው ተረሽነው፤ ሬሳቸው ሜዳ ላይ ተዘርግቶ፤ ህዝቡን ዕንባ እያራጨ ነበር።…ከዳሮ ጋር ሴቶች ሦስት ሲሆኑ ወንዶች ስድስት ናቸው። የአንድ ሴት ጡትና የአንድ ወንድ ብልት ተቆርጦ ወድቋል። መልካቸው እንዳይታወቅ ዓይናቸው ጠፍቷል፤ ፊታቸው ተጨፍጭፏል።…*

*የዳሮ ነጋሽ ሬሳ በህዝቡ ግፊት ወደ ሀኪም ቤት ተወሰደ። ሽል እንደያዘች አትቀበርም። ወደዚህ ዓለም ለመምጣት ጥቂት ቀናት የቀሩት ህፃን በሕይወት መኖር ያለመኖሩ መታወቅ አለበት። ምናልባት ለጉድ ቢተርፍስ?. . . ሕፃኑ ትንፋሹን ይዞ ከማህፀኗ ውስጥ ብቅ አለ። የእንግድነት ድምፁንም አሰማ። ይሁን እንጂ ብዙ አልቆየም። በመከራ ይዞአት የመጣው የሲቃ ነፍስ ወዲያው ጭልጭል ብላ ጠፋች።"* ***ተራሮችን ያንቀጠቀጠ ትውልድ****፤ ቅጽ አራት፤* 1991 *አዲስ አበባ።*

*ማርች* 8 *ዓለም አቀፍ ሴቶች ቀንን ስናስታውስ ከፆታ ጭቆና አልፋ ለሀገራችን ሕዝብ የዴሞክራሲ መብት መከበር ድምጿን ባሰማች የተረሸነችዋ የዘጠኝ ወር ነፍሰጡሯ ዳሮ ነጋሽ ከጎሊና የማትጠፋ የፋሽስቶችን የጭካኔ ደረጃ መስካሪ ታሪካችን ናትና ዘክረናታል።*

***<u>ድላይ፦ ውሻ ስታባርር የሞተች ይመስል</u>***




*በዱር በገደሉ በአሲምባ ተራራ ፋኖ ተሰማራ ብላችሁ ከወንድ ወንድሞቻችሁ በበለጠ ሁኔታ፤ መብታችሁ ተከብሮ፣ ሚናችሁ ታውቆ፣ ጀግንነታችሁ ተደንቆ፤ ትግሉን የመራችሁ፤ በደማችሁ አሲምባን ያደመቃችሁ፣ ኢትዮጵያዊነትን የፃፋችሁ ድላይና መሰል እህቶቻችን፣ ከሴቶችም አልፎ ለህዝብ መብትና ለሀገር አንድነት የተዋደቃችሁ ክብር ለናንተ ብለናል።*


*"…ድላይ የብዙኃን ኢትዮጵያዉያን ራዕይ ነች። መካሪ እህት አይዞን ባይ ጓዲት፣ ቆፍጣና ተጋዳይ፣ መረር ያለች የዕውነት ወታደር። ተርባ የደከሙት ይብሉ ብላለች፣ ተጠምታ የተጠሙት ይጠጡ ብላለች። በአጠጋቧ የተሰለፉት ወንድሞቿና እህቶቿ ሩህሩህ የመላው የኢትዮጵያ ሕዝብ ጓዲት፤ ለኢትዮጵያ ደግሞ ከወደቁት ብርቅዬና ትክ የለሽ ጀግና ልጆቿ አንዷ ድላይ። እንደ ስሟ ባለጥልቅ ትርጉም ድላይ - ፍላጐት (የነፃነት ፍላጐት) ድላይ - የድል ሴት።"* ***ድላይ*** *ከሚለው ጽሁፍ፤ ቴዎድሮስ ቺኪ*

*"በስልክ ተደውሎ "የአሲምባ ፍቅር" የሚል መጽሐፍ ፈልጊና አንብቢ የእህትሽን ታሪክ የያዘ መጽሐፍ ነው ስባል ልክ በህይወት መጣችልሽ የተባልኩ መሰለኝ ሲቃ እያነቀኝ ወደ መጻሕፍት ቤት ገሰገስኩ ስደርስም ለመጠየቅ አቃተኝ ሰውነቴ ተንቀጠቀጠ ከንፈሬ ሁሉ እየተርበተበተ መጽሐፍ ሻጯን ጠየቅኳት አለ ስትለኝ ልስማት አልኩና ደነገጥኩ እንደገና ከዚያም እራሴን ተቆጣጥሬ መጽሐፉን ተቀብየ ሳም አደረግሁት ሴትዮዋ በመገረም አየችኝ። ደፍሬ ግን ለማንበብ አልቻል አልኩኝ ደስታ ይሁን ሀዘን አላወቅሁም ዝብርቅርቅ ያለ ስሜት ተሰማኝ ከዚያም ለ*4 *ቀናት ያክል አመመኝ እና ተኛሁ እንደደርሳነ ሚካኤል አቅፌው ተኛሁ ከዚያም እራሴን አረጋግቼ ማንበብ ጀመርኩ::*

ምንም እንኳ የምትወዳቸውን ጓደኞችህን እና ያሳለፍከውን የውጣ ውረድ ዘመን እያሰብክ ሰላም ባይሰማህም ለእናትና አባትህ እንኳን እግዚአብሔር አተረፈላቸው ከነሱም አልፎ ለእኔና እኔን መሰል ያለ ታሪክ የቀሩ ቤተሰቦች ላሏቸው ሲል አምላክ እንኳን ከዚህ ቀን አደረሰህ። እህቴ መሞቷ ብቻ ሳይሆን የታሪክ ተካፋይ ባለመሆኗ አእምሮዬ ቆስሎ ይኖር ነበር።

በአፈ ታሪክ ታጋዮች ሁሉ ጀግንነቷን ያላትን ጥሩ ስነምግባር ይተርኩልኛል ነገር ግን የታሪክ መዝገብ ላይ አላሰፈሯትም። ከከተማ ሳይወጡ በቀይ ሽብር የተረሸኑት ደርግ እንደተደመሰሰ በቤተክርስቲያን መቃብር ቤት ተገንብቶ ከተረሸኑበት አጽማቸው ወጥቶ በክብር እንደገና ተቀበሩ እናም የቀይ ሽብሮች መቃብር ቤት ሲታይ ቤተሰቦቻቸው አልቅሰውም ሆነ ስቀው የልጆቻቸውን ታሪክ ያወሳሉ። ሌሎች ደግሞ በበረሃ የተሰውት ደግሞ የሰማእታት ሐውልት ተብሎ በተገነባው ውስጥ የአንድ ታጋይ ስሙና ትውልዱ የሰራው ታሪክ የተሰዋበት ቦታ ሁሉ በዝርዝር ይገኛል። የእኔ እህት ግን ውሻ ስታባርር የሞተች ይመስል የታሪክ መዝገብ ላይ ስሟ የለም አንዳንድ ታጋዮችን ሳነጋግራቸው እሷ የተሰዋችው ብአዲን ሳይመሰረት በኢሕአፓ ዘመን ነው ይሉኛል፤ ኢሕአፓ የውጭ ዜጋ ይመስል። እናም አእምሮዬ ሲደማ የቆየበት ታሪክ ዞሮ በአሜሪካ ሲመጣ ከቁስሌ ተፈወስኩ።" ድርብ ምናለ፤ የድላይ እህት

***<u>ሶፍያ አየለ፦ "5.10 "ትወገድ"</u>***




ሶፊያ አየለ ገብረመስቀል ዕድሜዋ 22 ዓመት፤ ሥራዋ የአዲስ አበባ ዩንቨርስቲ ተማሪ አድራሻዋ አዲስ አበባ ከተማ ከፍተኛ 15 ቀበሌ 30 ነበር። ሶፊያ በ1968 ዓ.ም. መጨረሻ ላይ ለ"ሕገወጡ" የኢሕአፓ ቡድን ተመልምላለች ተብሎ በየካቲት ወር 1970 ተይዛ ታሠረች። በደርጉ ምርመራ ክፍል በሻለቃ ብርሃኑ ከበደ የተፈረመ መግለጫ ለቋሚ ኮሚቴ የህገርና የሕዝብ ደህንነት ጉዳይ ኃላፊዎች "አደገኛ ፀረ-አብዮተኛ ስለሆነች የማያዳግም እርምጃ ሊወሰድባት ይገባል" ከሚል አስተያየት ጋር ግንቦት 1 ቀን 1970 ቀረበ።

በምርመራ መግለጫው የውሣኔው አምድ ስር የሚከተለው በደረጃ ታዘዘ።

ኮለኔል ካሣሁን ታፈሰ፤

ፍፁም የለየላት ቀንደኛ ፀረ-አብዮተኛ ስለሆነች አብዮታዊ ቅጣት ይገባታል። ለውሳኔ ለዋና ፀሐፊ ይቅረብ። 4.9.70

ሻምበል ፍቅረስላሴ ወግደረስ፤

ሕዝብ ደህንነት ባቀረበው መሠረት ትወገድ።4.9.70

ኮለኔል ካሣሁን ታፈሰ

ጓድ ሻለቃ ብርሃኑ፤ በዚሁ መሠረት ይፈፀም።4.9.70

ሻለቃ ብርሃኑ ከበደ፤

በውሳኔው መሠረት እንዲፈፀም ይሁን።4.9.70"

በወንጀል የተቀጡ ሰዎች መመዝገቢያ ካርድ ላይ "በወንጀል መዝገብ ቁጥር ሰ-111 በ4/9/70 በሞት ተቀጣች" ተብሎ ተመዘገበ።" ***ደም ያዘለ ዶሴ፤*** የልዩ ዐቃቤ ሕግ ጽ/ቤት፤ ጥር 2002 አዲስ አበባ።

በደርግ አገዛዝ ፊርማም ጥይት ነበር። ሶፍያ አየለና መሰል የያ ትውልድ ሴቶች ለተነሳችሁበት ዓላማ ጽናትና በቆራጥነት በከፈላችሁት መስዋዕትነት ቆመን እንድንሄድ አድርጋችኋል፣ ሕይወት ዘርታችሁብናልና ምስክርነታችን ይድረሳችሁ። በትግል መሞት ሕይወት ብላችሁ ገድላችሁን እንዘግብ ዘንድ ብዕር ሆናችሁናልና ትውልድ አይረሳችሁም።


***<u>ከእናቶች ማኅደር፦</u>***

የኢትዮጵያ እናቶች በአስከፊው ፋሽስታዊ የደርግ 17 ዓመታት አገዛዝ ከፍተኛውን መከራና እንግልት የተቀበሉ ናቸው። አቅፈው ያልጠገቧቸውን ልጆቻቸውን በድን በራፋቸው ላይ በገዳዮች ተጥሎላቸዋል። ተስፋቸውን የደርግ ጥይት በልቶባቸዋል። ክንዴ ልጃቸው፣ ፍቅር ሕይወታቸው በሀዘንና በእየዬ ተውጧል። ይህንን ሁሉ መከራና ስቃይ ተቀብለው አረመኔውን ፋሽስታዊ አገዛዝ ለመታገል ሀዘን በሸበሸበው አካላቸው የተሰለፉና ቀሪ ልጆቻቸውን ያበረታቱ ቀላል አልነበሩም። ትግሉ በሕዝብ ድል ይጠናቀቅ ዘንድ የፈሰሰው የልጆቻቸው ደም ገደብ የሌለውን የሰው ልጅ መብት ያመጣ ዘንድ፣ የተከሰከሰው የልጆቻቸው አጥንት፤ የሕዝብ መንግስት ዋልታና ምሰሶ ይሆን ዘንድ ከማበረታታት አልፈው ያታገሉ እናቶች ቀላል አልነበሩም። ለአብነት ያክል ከበርካታ እናቶች ጥንካሬ፣ ትዝታ፣ አሳዛኝና መሪር ሀዘን ታሪክ እጅግ ጥቂቱን በያ ትውልድ እናቶች ስም ለዛሬ እናቶችና ለትውልድ እነሆ!!!

***<u>ወ/ሮ ጥሩወርቅ ወልደሰማያት፦ «ወድቆ እንዳይቀር አርማዋን ከፍ! አርገሽ ቀጥይ»</u>***



ክ15ቀ35 ወ/ሮ ጥሩወርቅ ወልደሰማያት



ክ15ቀ35 ፀጋዬ እሸቴ Tsegaye Eshete

የካቲት 18 ቀን 2007 ዓ.ም. ከዚህ ዓለም በሞት የተለዩት የጀግናው ፀጋዬ እሸቴ እናት ወ/ሮ ጥሩወርቅ ወልደሰማያት በከፍተኛ 15 ቀበሌ 35 ዑራኤል ቤተ ክርስቲያን አካባቢ ነዋሪ ነበሩ። ወ/ሮ ጥሩወርቅ በ1969 ዓ.ም. መጨረሻ አካባቢ የጠፋው ፀጋዬ የበኩር ልጃቸው ሲሆን የልጃቸው መጥፋት ያላሸበራቸው እንደውም ጥንካሬአቸውና ምክራቸው ለሌሎች ብርታት የሆነ ቆፍጣና እናት ነበሩ።



ክ07 ብስራት ገብሬ H7 Bisrat Gebre


"ሚያዝያ 8 ቀን 1969 ዓ.ም. እህቴ ብስራት ገብሬ ተገደለች። መገደሏን እንደሰማሁ ቁጭትና ሀዘን ውስጤን እየበላሁ የፀጋዬ እናት ጋ ሄድኩኝ። የእህቴን መሞት ነገርኳቸው። ዓይኔ የቋጠረውን እንባ ዱብ ዱብ እያደረግሁ 'ብስራትን ገደሏት' አልኳቸው።

'እ...ና... ትግል እስከ ሞት አይደል?' አሉኝ። ቆፍጠን ባለ ስሜት። ቀጠል አደረጉናም 'እህትሽ ሞተች ታዲያስ ምን ትሆኚ? ትግሉን ቀጥይ፤ አንቺ ብቻ ነሽ እህት ያለሽ? ምነው በቀደም እዚህ ዑራኤል ቤተ ክርስቲያን በራችን ላይ ገድለው የጣሉትን አይተሽ የለም? እና እሱስ እህት የለውም? እናት የለውም? አለው። በእሱ ሞት 'አርማውን አነሳለሁ!' አይደል ያልሽኝ። እና ለብስራትስ ምን አዲስ

ነገር ተገኘ? በይ! ይልቅ ወድቆ እንዳይቀር አርማዋን ከፍ! አርገሽ ቀጥይ የምን ለቅሶ ነው. . .' ሲሉኝ እውነት ለመናገር ጠላኋቸው ተናደድኩባቸው። እህቴ እኮ ነች ብስራት።

በቀጣይነት የበኩር ልጃቸው ፀጋዬ እሸቴ 1969 ዓ.ም. መጨረሻ ገደማ መያዙንና ተስፋ እንደሌለው በተገናኘን ወቅት መዝገብነሽ (ሒሩት) ነገረችኝ። አዘንኩ እጅጉን ውስጤ ተቃጠለ። የብስራት ሲያንገበግበኝ የልጅነት ባለቤቴ የፀጋዬን ደግሞ ሰማሁ። ወደ ፀጋዬ እናት ሄድኩኝ። ልደብቃቸው አልፈለኩም።
'እማማ ፀጋዬንም ይዘውታል ተስፋ ያለውም አይመስል' አልኳቸው።
'እንዴት?' አሉኝ። 'አይ ሁኔታው ጥሩ አይደለም ከበድ ያለ ነው' ስላቸው አቋርጠውኝ
'ምን ያደርጉታል ብለሽ ነው? ምንም አይሆን ከመሞት በቀር፤ አይዞሽ ይልቅስ መርበትበቱን ትተሽ ትግሉን ቀጥይ' አሉኝ።
ቀጠል አድርገውም 'እሱ ከወደቀ ጠመንጃውን አንስተሽ መቀጠል ነው' ሲሉኝ እጅግ እራሴን ወቀስኩት። የእህቴን መሞት ስነግራቸው የሰጡኝን ምላሽ ለልጃቸውም ደገሙልኝ። እጅግ አከበርኳቸው። ምክራቸውና ጥንካሬአቸው ሁሉንም አስረስቶኝ የእህቴ ብስራትና የልጅነት ባለቤቴ ፀጋዬ ተከታታይ ሞት ሀዘንን ሳይሆን ብርታትን በወ/ሮ ጥሩወርቅ በኩል አጎናጽፎኝ ወደፊት ተጓዝሁ። ዛሬ በጥቂቱም ቢሆን ስለኚህ የጀግና እናት ብቻ ሳይሆኑ ጠንካራና ጀግና እናት ምስክርነቴን በመስጠት ስማቸው ይታወስ ዘንድ በማድረጌና ከእናቶች ለእናቶች መልዕክቴን በያ ትውልድ ስም በማስተላለፌ አመሰግናለሁ።" አልማዝ (እህተ)።

***<u>ወ/ሮ አበበች ተረፈ፦ «የሕዝብ ልጅ ነኝ»</u>***


መለስ ጥላሁን

". . . ከሰላምታ በኋላ ከዓመታት በፊት ስለተፈጸመው ሁኔታ ማውጋት ጀመርን አንገፈገፋቸው። «…ልጄ እንዲህ ከሰውነት ተራ የወጣሁት…በሽተኛ ሆኜ የቀረሁት ከልጄ ሞት በኋላ ነው። ያንን ዘመን ያንን ጊዜ ማሰብ አልፈልግም። እሸሸዋለሁ…በጣም እሸሸዋለሁ ነገሩ ግን ይከተለኛል። አልተወኝም እስቲ አሁን ለምን አነሳህብኝ?» ብለው ጠየቁኝ…ከገለፃዬ በኋላ ተግባባን ፈቃደኛ ሆኑ።

በረጅሙ ተነፈሱ…አሰቡ…«መቼም መሰለን ታውቃለህ ልጄ ጉበዝ…ልባም ነበር። በእጃቸው ቢወድቅም ደፋር ነበር። ይሄውልህ እሱ በልጅ አንደበቱ ያለኝን ነገር እኔን ለጉድ ጎልቶ እያሳየኝ ነው። «… አቡ! አንቺ እኮ ብትወልጂኝም… ለፍተሽ ብታሳድጊኝም … ብታስተምሪኝም … አንቺን ብቻ ልጦር፣ ዘመዶቼን ብቻ ልጠቅም ሳይሆን የተማርኩት ለሀገርና ለወገን ነው። እኔ እኮ ከእንግዲህ የሕዝብ ልጅ ነኝ» አለኝ። …

«… ወይኔ ልጄ አብሬው አበድኩ … ድምፁን ተከትዬ ባዘንኩ … አልሆነልኝም። መሬቱን ጧጥኩ … ለስንቱ ታቦት ተሳልኩ … በተጋዘበት ሁሉ በሰው አገር ተሰደድኩ። መጨረሻ ቀሙኝ … ብልህ ልጄን … መሰለ እኮ እንደሚሞት ያውቅ ነበር። አንድ ጊዜ ልቤ እየፈራ በየጊዜው ስለምወተውተው «እማዬ ዓላማ እኮ ነው! ብሞት እንኳ እንዳትፀፀቺ የኛ ደም ዛሬ ወንጀል እንደፈፀምን በከንቱ ቢፈስም ነገ ማርና ወተት ሆኖ ይፈለጋል …» አለኝ። «ያቺ አንደበት ተዘጋች» ብለው አለቀሱ። ስሜቴን መቆጣጠር አቃተኝ።

«… ወይ ልጄ! … መስዬ አረቄ ቀቅዬ ጠላ ጠምቄ ያሳደግሁት የደሀ ልጄ እንደ ውሻ ሜዳ ላይ ተጣለ …» ሀዘኑ ረታቸው አነቡ። …

... አንዴ ዲላ ... አንዴ ክብረ-መንግሥት ... አንዴ ቦረና ዋና ኢሕአፓ ነው ብለው እንዳገላቱት ... እንዳሰቃዩት ... አንድ ቀን እንኳን ልቡ ረግቶ ቀዝቃዛ ውሀ ሳይጠታ አውጥተው ደፉት። ... ነሐሴ 11 ቀን የቡሄ ዳቦ ይገፎለት ልሄድ ደፋ ቀና ስል ውዬ ... ለሊቱን ለ12 አጥቢያ ገደሉት። አለቀሱ ... «ከዚያማ ምን እልሀለሁ ይሄ ቤት ዙሪያው ተከበበ ሦስት ቀን ሙሉ ሰው እንዳይገባ ሰው እንዳይወጣ ... እንዳናለቅስ። የፈሰሰ ዕምባ ወደ ዓይን ይግባ ብሎ ማዘዝ ነው የቀራቸው። ...” ***ያልታደለው ትውልድ እውነተኛ ታሪክ መጽሐፍ፤ አብዲ አብዱላሂ።***

***<u>እማማ፦ «ሁልሽም ማማሰያሽን ይዘሽ ውጭ»</u>***


ከ15ቀ27 እማማ




“እማማ በከፍተኛ 15 ቀበሌ 27 ነዋሪ የሆኑ የጀግኖች እናት ብቻ ሳይሆኑ ጀግና የኢሕአፓ ደጋፊ ናቸው። ...

እማማ በቅላታቸው ላይ የተሸበሸበው ቆዳቸው ጭል ጭል ከምትለው ዓይናቸው ጋር ነጠላቸውን ተከናንበው ዘምቢላቸውን ይዘው ወደ ገበያ ሲወጡ ብርታት ይከተላቸዋል ፈገግታ ያጅባቸዋል ተስፋ ይከተላቸዋል። በዘምቢላቸው ያጨቁትን የ“ዴሞክራሲያ ሽንኩርት የተፈለገው ቦታ ያደርሳሉ። የልጆቻቸውን የድርጅት ሰነዶች በጥንቃቄ ያስቀምጣሉ። ቤታቸውን ቀን ለስብሰባ ማታ ለ“ዴሞክራሲያ ማባዣ ሰጥተዋል። ገቢ ወጪውን ይቆጣጠራሉ። አካባቢውን ይቃኛሉ። ሀዘን ግና ውስጣቸውን በልቶታል። ተንገብግበዋል።

በ1969 ዓ.ም. ጥር 26 ቀን ፋሽስቱ መንግስቱ ኃ/ማርያም ብርጋዴር ጀነራል ተፈሪ ባንቴን ጨምሮ ሰባት የደርግ አባላትን በመግደል “አብዮታችን ከተከላካይነት ወደ አጥቂነት ተሸጋገረ” ብሎ ባቅራራ ማግስት መኢሶን በመላዋ አዲስ አበባ ባደረገው የመንገድ ላይ ግድያ በርካታ ወጣቶችን በየአካባቢው ረሽኗል። በአዲስ አበባ ዩንቨርስቲም በርካታ ተማሪዎች በመኢሶን ክላሽን ታጭደዋል።

በዕለቱ በነበራቸው ቀጠሮ መሠረት መኳንንት አዳሙ፣ መስፍን ይጥና፣ ሰለሞን አማኑኤል እና አመነው ነገደ ዑራኤል አካባቢ ይገናኛሉ። የአሥመራን መንገድ ይዞ ቁልቁል ወደ መገናኛ እየተንቀሳቀሱ እንዳሉ የመኢሶን ገዳይ መኪና ታያቸዋለች። በውስጡ ካሉት የመኢሶን አባላት ውስጥ የዑራኤሉ መኢሶን መስፍን ዓለሙን መኪናዋ ቀስ ብላ አጠገባቸው ስትቆም መኪናው ውስጥ ያዩታል። እንዲቆሙ ትዕዛዝ ቢሰጣቸውም ሁሉም በተለያየ አቅጣጫ መሮጥ ይጀምራሉ መስፍንና ሌሎች የመኢሶን አባላት የተኩስ ሩምታ ይለቁባቸዋል። ሦስቱ ወጣቶች እዚያው መንገድ ላይ ሲገደሉ አመነው ነገደ ያመልጣል። ለወሬ ነጋሪ ተርፎ የሦስቱን ጓዶቹን አሟሟትና ማን እንደገደላቸው ለመናገር ይበቃል። አመነው ነገደ በኋላም አሲምባ ገብቶ ማህፀንት ጦርነት ላይ እንደተሰዋ ይነገራል።

መኢሶኖች የገደሏቸውን ወጣቶች አስከሬን ወደ ምኒልክ ሆስፒታል በጊዜው በሌሎች አካባቢ እየተዘዋወሩ ከረሸኗቸው ጋር ይደባልቃሉ። አንዱ በአንዱ ላይ የተከመረውን አስከሬን ለመለየት መታወቂያቸው ኪሳቸው ውስጥ የተገኙ አስከሬኖች ውስጥ እግራቸው ላይ በስቴፕለር መታወቂያው ተመቷል። መኳንንት አዳሙ እማማ ያሳደጉት የልጃቸው ልጅ ነው። እምቡጥ አበባቸው በባንዳዎች ተቀጥፎባቸዋል። ጀግና ልጃቸው አባከነ ለተባለው ጥይት 250 ብር ከፍለው ከምኒልክ ሆስፒታል

*ተረክበዋል። እማማ የልጃቸውን ዓርማ ከፍ አድርገዋል። አልተበገሩም። በእርጅና ዕድሜያቸው ከአቅማቸው በላይ ያበረከቱ እናት ናቸው።*

የቀበሌ 27 ሕዝባዊ ስብሰባ ላይ ተነስተው ወደ መድረኩ ወጡ

*"ወገኖቼ" አሉ ለስለስ ባለ ድምፃቸው "ወገኖቼ ልጆቻችንን ሰጠን የቀሩትንም መግቢያ መውጫ አሳጧቸው፣ የት እንድረስ፣ ሰው በሀገሩ፣ ሰው በሰፈሩ፣ እውን እነኚህ አብረውን ኖረዋል? አብረውን በልተዋል? አብረውን ጠጥተዋል? ምነዋ ልጅ ማየት አስጠላቸው? ምነዋ ልጅ ሲያዩ ይጐመዝዙ? እኛው መርጠናቸው እኛኑ ያሳድዳሉ። ልጆቻችንን ከእቅፋችን እየገደሉ የተረፉትንም እያሳደዱ ብቸኛ አድርገውናል። ስንበላ ስንጠጣ ትካዜ ነው፣ ለሊት የነሱን ኮቴና ኮሽታ ስናዳምጥ እንቅልፍ የለም፣ ወጣት ፍሊጋ ቤታችንን ይዞሩታል፣ የት እንድረስ የት ይሂዱ? ወገን ኧረ በቃን! ተነሱ! ከዚህ በላይ ምን ልንሆን ነው? በሀገራችን በቀያችን፣ በመንደራችን መኖር ከነሱን የሚፈለገው ሁልሽም ማማሲያሽን ይዘሽ ውጭ፣ ሀገራችን ለልጆቻችን ካልሆነች ምን ሕይወት ይኖረናል ኀበዝ ተነሱ! እንነሳ!..."*

*እያንዳንዱ የንግግራቸው መቋጫ አዳራሹን በጭብጨባ አናወጠው። እማማ የልባቸውን ተናገሩ፣ ደስ አላቸው፣ በእናትነት ድምጻቸው ለስብሰባው ድምቀት ሰጡት፣ ሞራል አጎናጸፉት፣ ተስፋና መተማመንን አጎናጸፉት።"* ***ፍፁም ነው እምነቱ ቀይ ሽብር የከፍተኛ 15 እውነተኛ ታሪክ መጽሐፍ፤ መስከረም 2007 ዓ.ም. ነሲቡ ስብሐት።***

*«ያ ትውልድ ተቋም» ማርች 8 ዓለም አቀፍ የሴቶች ቀንን ስናስታውስ የሴቶች እህቶቻችን የትግል ታሪክ ለቀጣይ ሴቶችና አዲስ ትውልድ ትምህርት ይሆን ዘንድ በማስገንዘብ ነው። ሀገራችን ኢትዮጵያ አንድነቷን ጠብቃ ያንዣበበባትን የዘር ፖለቲካ ልትወጣ የሴቶችን ጠንካራ ተሳትፎ ትፈልጋለች። አሁን ባለው አገዛዝ እስከ መታሰርና መገደል የደረሱ በርካታ ሴቶች እህቶቻችን ስቃያቸው ለሀገርና ሕዝብ ነውና ክብር ለናንተ እንላለን። የአሁኑ ትውልድ ወጣት ሴቶች የሀገራችሁን ታሪክ መርምራችሁ ከእናንተ በፊት ከነበሩ ቀደምት ሴት ታጋዮች ጠንካራና ደካማ ጐን ትምህርት ቀስማችሁ ኢትዮጵያን የሁሉም ዘሮች ቤት ታደርጓት ዘንድ ይጠበቃል። "ሽመንደፈራ" እንዳለው ዜመኛ ኢትዮጵያ ቤታችን ለእስላሙም ለክርስቲያኑም አትጠብም። የትግሉ እመቤቶች በማርች 8 ክብረ ባህል ዕይታችሁ ሀገራችሁ ትሁን፣ ጨኸታችሁ ለሁሉም ዘር ሲሆን ኢትዮጵያዊነታችን ከፍ ይላል። ኢትዮጵያዊነት ብሔራዊ ስሜት ዳግም ይታደሳል።*

*«ያ ትውልድ ተቋም» ዓለም አቀፍ የሴቶችን ቀን* (*ማርች* 8) *ስናከብር፤ ሴቶች ማኅበራዊ ሕይወትን ጨምሮ ለመብትና ለነፃነት በተደረገው ተጋድሎ ያስመዘገቡት ታሪክና የተጫወቱት ሚና በሚገባ የተዘገበ አለመሆኑ ከአሁኑ ትውልድ ጋር የታሪክ ክፍተት ፈጥሯል እንላለን። «ያ ትውልድ ተቋም» የኢትዮጵያ ሴቶችን የትግል ታሪክ በማሰባሰብ የአሁኑና መጪው ትውልድ ይመራመርበት፣ ያጠናበት፣ ይጽፍበት፣ ይማርበት ዘንድ የሚደረገው ጥረት የሁሉንም ትብብር ጠያቂ መሆኑን በዚህ አጋጣሚ ማስገንዘብ እንወዳለን።*

*የደርግ ገዳዮች ትውልድ ፈጅነታቸውን አድምቀን ልናሰምር የምንገደደው ለቂም በቀልና ለቁርሾ ሳይሆን የፈጸሙት አሳፋሪ ድርጊት ዳግም እንዳይደገም ትውልድ ይማርበት ዘንድ አስፈላጊ መሆኑን እናምንበታለንና ነው። በተጨማሪም በግፍ የተጨፈጨፉ የያ ትውልድ ፈርጦች ታሪክ ሲተርኩት እያሳዘነ፣ እያስደመመ፣ እያስለቀሰ፣ እያኮራ፣ እያሳቀ፣ በትዝታ ፈረስ እያስጋለበ፣ እያስቆጨ፣ እየጣፈጠ፣ ሌላም ሌላ የሚነኑድ አኩሪና ህያው ታሪክ ነውና ስንጽፍ፣ ስንናገር ብንውል፣ ብናድር አናፍርበትምና ክብር ለያ ትውልድ ወገኖች እንላለን።*

**በኢትዮጵያ የትግል ታሪክ ከያ ትውልድ እንቅስቃሴ ጀምሮ በቀይ ሽብርና በአሁኑ ወቅት መስዋትነት ከከፈሉት በርካታ እህቶቻችን ምስል በ<<ያ ትውልድ ተቋም>> ድረ ገጽ** ([www.yatewlid.com](http://www.yatewlid.com), [www.yatewlid.org](http://www.yatewlid.org) ) **የተካተተ።**


አበራሽ በርታ
Aberash Berta


አበራሽ ሰይፉ
Aberash Seifu


አበበች ካሣ
Abebech Kassa


አልማዝ ዓለማየሁ
Almaz Alemayehu


አልማዝ ሽፈራው
Almaz Shiferaw


አልማዝ ጣፋ
Almaz Tafa


አልማዝ
Almaz


አንቀጸ ተገኝ
Anqese Tegene


አስቴር ደገፉ
Aster Degefu


አስቴር ዘውዴ
Aster Zewde


ዓይናለም በቀለ
Aynalem Bekele


ብሥራት ገ/ጊዮርጊስ
H07 Bisrat G/Giyorgs


ዳሮ ነጋሽ
Daro Negash


ስመኝ ምናለ
ድላይ


እጅጋየሁ ደበላ
Ejigayehu Debela
ከ09ቀ09


ገነት ክፈለው


652. መዝገብ ነሽ አባያ
ጎሕ መጽሔት ም/አዘጋጅ


ማርታ መብራቱ
Marta Mebrahtu



ሜሮን አሰፋ


ምርአት አስግድ









በትግል መሞት ሕይወት
ባመጻ መሞት ሕይወት
ዳግም ትንሳኤ ልደት
የደም የድል ጎዳና
የነቼ የነሆ ፋና
የፋኖነት ምስራቹ
የታጋይነት ብስራቱ
ድል ተቀዳጅቶ መሞቱ
በሞት ሕይወት ማግኘቱ
እናንት የአብዮት ሰማዕታት
የነገ ድል ቀን ህያዋን
የነጻነት ቀይ ጮራዎች
የጭቁን ሕዝቦች ተገን
በወህኒ ሲቃ ሰቆቃ
በፋሽስቶች ጥይት ጅራፍ
በመወገር በመገረፍ
በመታደን በመጨፍጨፍ
በቆረሳችሁት ስጋ

በደማችሁት የደም ጎርፍ
የስርዓቱ እድፍ ይታጠባል
የፋሽስት ጀሌ ይደቃል
ባንዳ በደሙ ይሾቃል
ጭቁን ድሉን ይቀዳጃል።

በሴቶች ተሳትፎ የኢትዮጵያችን አንድነት ያብባል!!

ማርች 8 ሰማዕታት እህቶቻችን ሚታወሱበት!

**«ያ ትውልድ ተቋም»**

**የካቲት 29 ቀን 2012 ዓ.ም. (March 8, 2020)**

ኢሜል :yatewlid@gmail.com

ድረ ገጽ : http://www.yatewlid.com , http://www.yatewlid.org

ምስለ ገጽ: yatewlid